# ★ ዴሞክራሲያ ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞክራሲያ ቅፅ 40 ቁ. 8 ግንቦት 2007 ዓ.ም


## ወርሃ ግንቦትን ስናስታውስ

በአጋጣሚም ይሁን ወይም የራሱ ዕጣ ፈንታ ሆኖበት እንደሆን በማይታወቅ ምክንያት ፤ ከአለፉት ሰባ(70) ዓመታት ጀምሮ የሚፈራረቀው ወርሃ ግንቦት፤ ለሀገራችን የሚበጃት ወር አልሆነም ። ምንችክ - ድርቅ ብሎ ሀገራችንን ለጥቃትና ለወረራ ፤ ለጦርነትና ለጭቆና አገዛዝ የሚያጋልጣት ወር በመሆን ይታወቃል። ግንቦት ለኢትዮጵያ በተደጋጋሚ ችግር የሚያመጣባት ወር ሆኖ ቆይቷል። አሁንም ቢሆን፣ ግንቦት ወር የሀገራችን ባላንጣ ወር መሆኑን ቀጥሎበታል። ለካ በባህሉ፣ ሕዝቡ፣ "አገመገመ ሚያዝያና ግንቦት ያለው ሊበላ የሌለው ሊሞት!" እያለ የሚያጉረመርመው ወዶ አይደለም!

ይህ የግንቦት ወር የሚያመጣብንን የአዚም አዙሪት ለመስበር ግን ግዑዝ በሆነው ወር እያመካኘን መኖር የሚገባን አንዳልሆነ እንረዳለን። ግንቦትን እየጠበቀ የሚፈራረቅብንን መከራና ስቃይ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ተረድተን በማወቅ ሌላ መዘዘኛ ግንቦት እንዳይመጣብን ተግተን መሥራት ይጠበቅብናል። እንደ ቃልቻ በወራት፤ እንደ ኮከብ ቆጣሪ በዘመናት፤ እንደ ሞራ ገላጭ በምትሃት እያመካኙ ለመኖር፤ የ21ኛው ክፍለ ዘመን ህይወትና ሂደት አይፈቅዱም።

ለታሪክ ግንዛቤ የሚረዳ ከሆነ ግን፤ ለአለፉት ሰባ(70) ዓመታት በሀገራችን ላይ የተፈራረቁት የግንቦት ወራት፤ ያመጧቸውን መከራዎች፣ ጥቃቶችና ውርደቶች በየፈርጃቸው አስታውሶ መመዝገቡ አግባብነት ይኖረዋል ብለን እናምናለን። የዚህ ጥረታችን ዓላማው፣ ሌላ መከራና ስቃይ እንዳይመጣ ለመከላከልና ለስቃያችን ምክንያቶችና፤ የመከራችን ጎታቾች የሆኑትን ጠላቶቻችንን አውቀን ተባብረን በመቆም ለመከላከል እንድንችል ብቻ ነው።

በ1928 ዓም ግፈኛው የኢጣልያ ፋሽስት ጦር ሀገራችንን ወርሮ አዲስ አበባ የገባበት ወር ግንቦት ነበር። ከአምስት ዓመታት መራራ የነፃነት ትግል በኋላም፣ ጣሊያኖች፣ ከሀገራችን ጠቅልለው የተባረሩበት በ1933 ዓም ግንቦት ነበር። የኢትዮጵያ ዐርበኞች በመተባበር፤ ጣሊያንን ከሀገራችን ጠራርገው ያስወጡበት ወርም ግንቦት 1933 ዓም እንደ ነበር በታሪክ መጽሐፍት የተመዘገበና በሕይወት ያሉም ዐርበኞቻችን ይናገሩታሉ።

የኢጣሊያ ወራሪዎች ከተባረሩ በኋላ፤ ከ1933 ዓም እስከ 1966 ዓም ድረስ ሀገራችንን ጨቁኖ የገዛው ሥርዓትም የተተከለው፤ ሚያዚያ ተገባድዶ በግንቦት ወር መባቻ ነበር። ደርግም በበኩሉ፣ አገዛዙን የተቃወሙትን ሀገር ወዳድ ጀኔራሎችና ዴሞክራሲያውያን የጦር መኮንኖችን በግፍ የረሸነበት ወር ግንቦት ነበር። የኢትዮጵያ ላብ አደሮች፤ የሠራተኛን ቀን (ሜይ ፈርስትን) ለማክበር ሰላማዊ ሰልፍ በመውጣታቸው ደርግ በአደባባይ የረሸናቸው በግንቦት/ሜይ ቀን ነበር። ለወያኔ አገዛዝ ሀገሪቱን አጋልጦ የሸሸበትም በዚህ አዚመኛው ግንቦት ወር እንደ ነበር ታሪክ መዝግቦታል። ወርሃ ግንቦትን እየታከከ የሚመጣውን የሀገራችንን መከራና ስቃይ ዘርዝረን አንጨርሰውም ። እንዲያው፤ በተፈራረቁት የግንቦት ወራት

ላይ ከማተኮር ይልቅ፤ ሌላ መርዝ ተሸክሞ ከሚመጣብን አዲስ ግንቦት ራሳችንን ለመከላከል፣ ምን ማድረግ ይኖርብናል ? የሚለውን ጥያቄ እየጠየቁ መፍትሄውን መፈለግ የወቅቱ አማራጭና ሀገራዊ ግደታም ነው እንላለን።

ወያኔ አዲስ አበባ የገባበት ወር ግንቦት ነበር። ደርግ ጥሏት የሸሻትን ሀገር ባዶዋን በማግኘቱ ወያኔ፣ የዘር ፖለቲካ በመዘርጋት የጥላቻና የመለያየት መርዝ የተከለበትና የሽብር ኢጋንንት በረት የከፈተበት በዚህ ግንቦት ወር ነበር። ወያኔ ከገባ እስካሁን ድረስ፤ ሃያ(24 ) ግንቦቶች እየመጡ ሄደዋል። በእያንዳንዳቸው ተፈራራቂ ግንቦቶች ተዘርዝረው የማያበቁ ወንጀሎች ተፈጽመዋል። የግንቦት ወር በመፈራረቅ በሀገራችን የሰው ልጅ ደም በግፍ የፈሰሰበት ወር በመሆኑም የሚታወቅ ነው።

በተፈራራቂዎቹ ግንቦቶች፣ የይስሙላና የማጭበርበሪያ ምርጫ ቲያትሮች ሲከናወኑ አይተናል። እነሆ በዘንድሮው ግንቦትም፤ ወያኔን እንደገና ዙፋን ላይ ለማፈናጠጥ ሽር-ጉድ እያለ ይገኛል። የጉልቻ መለዋወጥ ወጡን የሚያሳምረው ይመስል፤ የእርስ በእርስ ሹመትና ሥልጣን መተካካትና መሽጋሸግ እያደረጉ ሕዝቡን የሚያታልሉበት ወር ግንቦት ነው። የኃማ መርገጫ ማህተም የሆነው ፓርላማ ተብየው፣ አባላት ለስሙ የሚፈራረቁበትም በዚህ ጉደኛ ግንቦት ወር ነው። ምርጫ አካሄደናል ብለው ምዕራባውያን አለቆቻቸውን የሚደልሉበት ወር በመሆኑ፤ ግንቦት፤ ለወያኔዎቹ ትርጉም ሰጥቷቸዋል። በመሆኑም፤ "ግምቦት ግምቦተይ ፤ አቦይ መኣረይ ፤ አደይ ወላዲተይ !"

ግንቦት፣ ግንቦትየ፤
አባቴ ማሬ፣ እናቴ ወላጄ
እንደማለት ይመስላል። ታዲያ ግንቦትን እነሱ ቢያቆለጳጵሱትም ምክነያት አላቸው።

ይህም አልበቃ ብሎ ደግሞ፤ ይህ ያሳለፍነው የሚያዚያ ወርም፣ እንደ ግንቦት ዋዜማ እንዲታሰብ ተፈልጎ ነው መሰል፤ ሠላሣ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች በሊቢያ በረሃ አንገታቸውን የተቀሉበት ወር ሆኗል። "ሚያዚያና ግንቦት ተባበሩና ፤ ኢትዮጵያ ሆነች የወላድ መና" ተብሎ ወደፊት ሊጠቀስ ይችል ይሆናል! የሚገርመው ምጸት ግን፤ ወራት መተባበር ሲቻላቸው፤ እኛ ለመተባበር እስካሁንም ድረስ አለመቻላችን ነው። ሚያዝያና ግንቦት ሲተባበሩ፤ ፖለቲከኞች ተገትረው ቀሩ "እየተባለ ቢዘመርባቸው አያስደንቅም።

ሙታን ህያውን ለመግዛት እንደማይፈቅድላቸው ሁሉ፣ ወራትም እንደዚሁ፣ በሰዎች ላይ ወንጀል ለመስራት ሊተባበሩ ባልተፈቀደላቸውም ነበር። ቀን ሲከዳ፤ ሰማይ ምድሩ ይደፋል ብሎ ከመማረር ይልቅ፤ የቀንን ክኅደት ተቋቁሞ ለማሳለፍ፤ "ከአባት ከዳሚት" ጋር ተጋብቶም ቢሆን፤ ጠላትን ማቸነፍ ብልኅነት እንደሆነ ታሪክ ይጠቁማል። ክፉ ወራትን፤ ክፋታቸውን ከሚጠቀሙባቸው ጠላቶች ጋር ሁሉንም ለማጥፋትና ለማስወገድ፤ የተባበረ ኃይልና ጉልበት ማስፈለጉ ወሳኝ ነበር። የጊዜና የቦታ፣ የሁኔታዎችና ያጋጣሚዎች ተጠቃሚና ወሳኙ፣ ሰው እንጅ ወራት ሊሆኑ አይገባም ነበር።

እስካሁን ድረስ፤ ሰኔና ሰኞ፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አልተገጣጠሙለትም። ተገጣጥመውለትም ከሆነ እስከ ዛሬ ድረስ አልተጠቀምባቸውም። ለአለፉት አርባ ሁለት (42) ዓመታት፤ ሳይዘጋጅ፣ ሳይደራጅ በመቅረቱ፤ ሦስት ዕድሎቹን ግን ተነጥቋል። በላዒ ሰብ ሥርዓቶች በመፈራረቅ ገዝተውታል። እስካሁንም ቢሆን ሁኔታዎችን ለመለወጥ፤ አንዳችም አመርቂ ተግባር ስለአልተፈጸመ፤ ሌላው አራተኛ አጥፊ ግንቦት አይመጣም ብሎ ማለት አይቻልም። ምክንያቱም ሊመጣ የሚችልበትን ዕድል ለመዝጋት፤ የተደረገ አንዳችም መከላካያ ኃይል ስለ አልተበጀ ነው።

ዛሬ፣ አስቀድሞ ካልተዘጋጁ፤ ጊዜው ሲደርስ ሡርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ ማለት ሊሆን ነው። እንዲያውም ይግረማችሁ ተብሎ፤ ዛሬ በጎተራ ውስጥ በርበሬ ስለሌለ፣ ሁሉም በመርበትበት፤ ቃሪያ ለመትከል ሊገደድ ነው። "በርበሬ ቀንጥሱ!"

የሚለው የቆየው ብሂል ቀርቶ፤ "ቃርያ ትከሉ!" ወደሚል አነጋገር ተለውጧል። ቃሪያው ተተክሎ፣ ተኮትኩቶ፣ አድጎ፣ አፍርቶ፣ በርበሬ ሆኖ፤ ተቀንጥሶ፣ ተወቅጦ፣ ተደቁሶ፣ ለወጥ ማጣፈጫ ቅመም ሆኖ እስኪዘጋጅ ድረስ፤ ወያኔ ሥራውን ሰርቶ ወደ እሚሄድበት ይሄዳል።

ደርግም፣ ኢትዮጵያን አጥፍቶ ጠፋ እንጅ ኢትዮጵያን ከጥፋት ለመከላከል የሚችል ኃይል እስካሁን አልተገኘም። ሀገራችንም አጥፊዎቿን ማስተናገድ እንጅ፤ አርበኞቿን በመንከባከብ አታወቅበትም። በመሬቷም፤ አጥፊና ጠፊዎች ሲራኮቱ ይታያሉ እንጅ፤ አልሚዎችና አዳኞች አልተከሰቱላትም። ይህ አባባል፣ ከሞራል እሴት ባሻገር መገምገም ይኖርበታል።

በወቅቱ፣ በሰዓቱ የሕዝቡን ጥፋት መከላከል ካልተቻለ፤ የኢትዮጵያን ሙት-ዓመት ለማውጣት ቡታ መስደድ ሆኖ ይቀራል። ይህ አይሆንም ብለው ራሳቸውን የሚያታልሉ ካሉ፤ የሕዝቦችንና የየሀገሮቻቸውን ታሪክ ያልተገነዘቡ ብቻ ናቸው። የዓለም ታሪክና ሂደቱ ብዙ ሕዝቦችና ሀገራት፤ ቋንቋቸው፣ ሥልጣኔያቸውና ጎልውናቸው ፈልሶ እንደቀረ በታሪክ ድርሳናት ተመዝግበው እናገኛቸዋለን። ኢትዮጵያ ሀገራችንም ከዚህ ክስተት ነፃ ትሆናለች ብለን ራሳችንን ልንደልለው አንችልም። ኢትዮጵያን ከስር- መሠረቷ ለማጥፋት ጉዞው መጀመሩን መገንዘብ ያስፈልጋል። አስተዋይ ጎሊና ላለው ዜጋ፣ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር፣ ዜጎቿም እንደ አንድ ሕዝብ ሆነው ለመኖር ያላቸው ዕድል ከዕለት ዕለት እየጠበበ መሄዱን ሊገነዘብ አይችልም ብሎ ማመን ይከብዳል።

"የአንድ መቶ ዓመት ታሪክ ያላት ሀገር ነች" የሚሏትን ሀገር በአንድ መቶ ዓመት ውስጥ እንዳልነበረች ለማድረግ፤ ወያኔዎቹ 75 ዓመት ብቻ ቀርቷቸዋል። የከፋ መከራ በሀገራችን ሰማይ እያንዣበበ ነው ብለው ሲያስጠነቅቁ የነበሩ ልሂቃንና ሰማዕታት፤ ጩከታቸውን የሚሰማላቸው አጥተው፤ እያዘኑ ህይወታቸውን አሳልፈዋል። የሰማዕታቱ ጩኸት አሁንም በኢትዮጵያ አድማስ እያስጠነቀቀ ይገኛል። ሰሚ ማግኘቱን ግን አሁንም እንጠራጠራለን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የድረሱልኝ ጩኸት፣ የቁራ ጩኸት ሆኖ እንዳይቀር፤ በሕዝብ ስም እንታገላለን የሚሉ ሁሉ ሊያስቡበት ይገባል። ኢሕአፓም "እኔ አስቀድሜ ተናግሬ ነበር የሚሰማኝ አጥቼ ነው እንጅ" በሚል ተስፋ አስቆራጭ አስተሳሰብ ክንዱን የሚያለዝብበት ሳይሆን እንዲያውም በይበልጡኑ የድርሻውን ለመወጣት፤ የታሪክ አደራ የጣለበትን ኃላፊነት ሁሉ ተሸክሞ ስኬታማ እንዲሆን ከፍተኛ ጥረት ማድረጉን የሚቀጥልበት ነው።

አጥፊዎቿን ለማጥፋት፤ የሚደረገው ትግል አፅንኦት እየተሰጠው፤ መተኪያውም አብሮ ካልተሰበበት፤ ጥረቱ ሁሉ እየፈጩ ጥሬ ሆኖ ይቀራል። አንዳንድ ወገኖች፣ "ወያኔ መጀመሪያ ይውደቅ እንጅ፤ ከዚያ በኋላስ እንደፈቀደው ይሁን" ሲሉ ይደመጣሉ። ይህ ኃላፊነት የጎደለው አመለካከት ይመስለናል። ትላንትም "ደርግ ይውደቅ እንጅ ከሱ በኋላ የባሰ አይመጣም" ሲባል ነበር። ያ ግን ሳይሆን ቀርቶ፤ "ትሻልን ሰድጄ፤ ትብስን አመጣሁ" እየተባለ ነው ። ዛሬ ! አሁንም ዛሬ ካልተዘጋጀን፣ እንደ ትላንቱ እንደማንጃጃል ምንም ዋስትና አይኖረንም። ሁል ጊዜ እንዝህላልነት፤ ወደ መጃጃልና ትጥቅ ወደ ማስፈታት እንደሚያመራ ከተመከሯችን ተገንዝበናል። ልባም ሕዝብ ደግሞ በአንድ ጉዳይ ላይ መሳሳት ካለበት፤ ሊሳሳት የሚገባው አንድ ጊዜ ብቻ ነው። የፖለቲካ ቁማርተኞች ሁሉ ጊዜ እያታለሉት እንዲኖሩ ሊፈቀድላቸው አይገባም።

ለአለፉት 25 ዓመታት፣ ከመጀመሪያውንም ቢሆን፣ አምባገነንን ለመጣል በሚደረገው ትግል፤ የረባ ውጤት አልተመዘገበም። በተያያዘ መልኩ መተኪያውን ለማዘጋጀት ጥረቱ አብሮ ካልታሰበበት፤ ሀገሪቱን በአዲስ ጥርስ ለመጋጥ ላሰፈሰፈና ማንነቱም ላልታወቀ ጭራቅ አሳልፎ መስጠት ይሆናል። አንድ ሕዝብ ሰማይ - ምድሩ ተደፍቶበት ተስፋ ከቆረጠ፤ ሳይወድ በግድ፣ "ከማያውቁት መልዓክ፤ የለመዱት ሰይጣን ይሻላል" ከሚል ድምዳሜ ለመድረስ ይገደዳል። ከተጣለበት ቀንበር ለመላቀቀም አይጥርም።

የሌሎች ሀገራት ሕዝቦች፤ ከጭቆና ቀንበር ነፃ ለመውጣት ያደረጉትንም ትግልና ያገኙትን ውጤትም፤ እንደ አልፎ ሃጅ ዜና ከመስማት አልፎ -ተርፎ፤ እኔስ እንደነርሱ ታግዬ፣ ጨቋኙን አገዛዝ ለምን አላስወግድም ? ብሎ አይፍጨረጨርም። ይህ ደግሞ ድርጅቶች ነፃ ያወጡኛል በማለት፤ በቀቢፀ-ተስፋ መኖርን የመረጠ ይመስላል። መራራው ሐቅ ግን፤ እራሱ ታግሎ እራሱን ነፃ ካላወጣ ማንም መጥቶ ነፃ የማያወጣው መሆኑ ነው። በሕዝባዊ አመፅ ብቻ ነው ዘረኞች ሊወገዱ የሚችሉት።

በሌሎች ሀገራት የነበሩ አምባገነን አገዛዞች ሁሉ የተወገዱት በሕዝባዊ አመፅ እንጅ በአቤቱታና በልመና አይደለም። ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግና የተቃውሞ አቤቱታ ማሰማት፤ የትግሉ አካሎች መሆናቸው ባይካድም አመፀኛ አገዛዝ የሚወገደው፤ በሕዝብ አመፅ እንጅ፤ በወረቀት ጋጋታ፣ በሰልፍ ጫጫታ ብቻ አይደለም። በሚገባው ቋንቋ በማናገር ደግሞ ሳይወድ በግድ ለሁኔታው እንዲገዛ ይገደዳል። የመጨረሻው ድል አድራጊም፣ ሕዝባዊ አመፅ ብቻ ይሆናል!

"የባሰ እንዳይመጣ ሀገርከን አትልቀቅ" የሚለው አባባል ቀርቶ፤ "ወያኔ ከሚበላኝ፤ የአይሲስ ጎራዴ ይረደኝ ! የዱር አራዊት ይብላኝ! የውቅያኖስ ባህር ይዋጠኝ! " እያለ ወጣቱ ሁሉ በየአቅጣጫው እየተሰደደ ነው። የአገዛዙም ተግባር ለዚህ ሁኔታ ምቹ እየሆነ ይገኛል። ኢትዮጵያ ዛሬ ሰማይ ምድሩ የተደፋባቸው ዜጎች ሁሉ የታሰሩባት ምድራዊ ሲኦል ሆናለች። ወያኔም ትላንት የብሄሮች እስር ቤት ሲላት የነበረችውን ሀገር፤ ዛሬ ምድራዊ ሲያል አድርጓታል። የዜጎቿም ምርጫ በሁለት ተወስኗል። ስቃይ የበዛበት እስር ቤት ወይም ገሀነመ- እሳት የሚነድባት ምድራዊ ሲኦል ! ከነኝህ ሊያመልጥ የቻለው ደግሞ እየተሰደደ በቀጣይነት ለመብት አልባ ኑሮ፣ ለችግርና ስቃይ፣ ለተለያዩ አሰቃቂ ድርጊቶች መዳረግና አለፍ ሲልም በሚያሳዝንና በሚሰቀጥጥ ሁናቴ በዐረመኔዎች እጅ ለመታረድ በቅቷል።

መከራን ቢሸሹት እየተከታተለ ያጠፋል እንጅ ጭራሽ ሊለቅ አይችልም። የመከራን ገመድ በጥሶ ለመገላገል ካስፈለገ፤ መፍትሄው የችግሩ ምክንያት የሆነውን ከምንጩ ማድረቅ ብቻ ነው። የመከራው ሁሉ ምንጭ ደግሞ በዘርና በቋንቋ ተደራጅቶ፤ በባዕዳን ተደግፎ ሀገራችንን የሚያጠፋው ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ነው። ይህ አገዛዝ ካልተወገደ ኢትዮጵያ ሠላም ታገኛለች ማለት ዘበት ይሆናል። ሕዝቧም ፍትኅ ርትዕ አግኝቶ በነፃነት ሊኖር ከቶ አይችልም። የጠብመንጃ እሩምታ፤ የሰላዮች ጋጋታ ዘላቂ ሠላምን አያሰፍንም። ደርግም ሞክሮ አልተሳካለትም። ካለፈ ታሪክ አለመማር ደግሞ በዘለቄታ መልኩ እራስን እየረገሙ መኖር ነው ትርፉ።

የኢትዮጵያ ሕዝብም ይህንን እያየ፤ መራራ ሀዘኑን ለመሸከም የሚያስችለው አቅምና ትካሻ አጥቷል። በአንፃሩ ደግሞ ለአለፉት ዓመታት በቂ መራራ ተመክሮን አግኝቷል። ከተመክሮው ተምሮ መፍትሄ ለማግኘት ግን እስካሁን አልታደለም። የዚህ ሁሉ ጉድለት ተጠያቂነት ከማን ትከሻ ላይ እንደሚያርፍ ግን ኃላፊነትንና ተጠያቂነትን ለመቀበል የሚደፍሩ ድርጅቶችም ይሁኑ ተቋማት አይገኙም።

በተየያዘ መልኩ ግን አንዱ ሌላውን ለመንቀፍና፤ የራሱን ጉድለት ወደ ሌላው ለማላከክ ሲሯሯጥ ይታያል። የዚህ ሁሉ ተጠቃሚ የሆኑት ደግሞ አምባገነን ገዥዎች ናቸው። የሀገር ወዳድ የፖለቲካ ኃይላት አለመተባበርና አለመስማማት፤ ሁልጊዜ ለአምባገነን መሪዎች ሥርግና ምላሽ በመሆን የአገዛዝ ዕድሜያቸውን ያራዝምላቸዋል። የሕዝቡም የመከራ ኑሮ ደግሞ በገሃድ እንደሚታየው በከፋ መልኩ ይቀጥላል።

በአሁኑ ወቅት አስገራሚ ሆነው ከመጡት ችግሮች መካከል፤ ኢትዮጵያ ባለቤት ያጣች ሀገር መሆኗ ብቻ ሳይሆን፤ ችግሯን የሚያውቅላትና መፍትሄውን ለመፈለግ የሚችል ኃይል ማጣቷም ጭምር ነው። ሀገሪቱ "ሁለት ያጣ ጎመን" ምድር ሆናለች ቢባል ማጋነን አይሆንም። ምክንያቱም፣ በአንድ በኩል ችግሯን በትክክል የሚረዳላት ማጣቷ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ፤ መፍትኄ እናመጣልን የሚሉት ወገኖች፤ የመፍትተኄው ድርና ማግ ውሉ የጠፋባቸው መሆኑ ነው።

ለነገሩማ ችግሩን በሚገባ ሳይረዱ እንዴትስ መፍትኄ መፈለግ ይቻላል? የመፍትኄው ፍሊጋ ድሩና ማጉ ስለተሰወረበት፤ አብዛኛው እንደ ተደገመበት ጋኔል፣ በዳፍንት ወስጥ ገብቶ መደናበርን የመረጠ ይመስላል። ራዕይ ያጣ ኅብረተሰብ ለመሆናችን ምልክቱ፤ አቅጣጫ አመልካች ሀገራዊ ተቋምና ኃይል ማጣታችን ነው። አንዳንድ ድርጅቶች፤ የፖለቲካ ፕሮግራማቸው፣ ሀገራዊ ራዕይን ሊታካ ይችላል ብለው ይገምታሉ። ይህ ግምት ወደ አሳሳች ግንዛቤ ሊያመራ ይችላል።

የድርጅቶች የፖለቲካ ፕሮግራምና የአንድ ሀገር ስትራተጂያዊ ራዕይ በግልቡ ሲያይዋቸው ተመሳሳይ ሊመስሉ ይችሉ ይሆናል። ግን ልዩነት አላቸው። ሀገራዊ ራዕይ፣ የአንድን ሀገር ሕዝብ መሠረታዊና ዘላቂ ጥቅምን ከረዥሙ ርቀት አኳያ አማትሮ፤ ስትራተጂያዊ ንድፍን ያካተተ ሰነድ ማዘጋጀት ይመስለናል። ዓላማውም፤ የሀገሪቱን ሕዝብ ታሪክ፣ ባኅል፣ ዕምነት፣ የወደፊቱንም ተስፋና ምኞት የሚያንጸባርቅና የረዥም ርቅት ጉዞን የሚያካትትና አቅጣጫን አመልካች መሠረታዊ ሰነድ እንደሆነ ይታመናል። የሀገሪቱን የአገዛዝና የአስተዳደር ፍልስፍና፤ የዜጎቿንም ዘላቂ የህይወት መመሪያ ርዕዮትና የአብሮ መኖር ነፀብራቅ አመልካችና አረጋጋጭ ሰነድ ማለት ነው። አገልግሎቱና ጠቀሜታውም፤ በወቅቱ ያለውን ትውልድ ጥቅም ለማስጠበቅ ብቻ ሳይሆን፤ ከትውልድ ትውልድ ለሚተላለፈውም ዜጋ እንዲጠቅም ሆኖ የሚሰናዳ ቋሚና ነዋሪ ሊሆን ይችላል። ለሀገሪቱ ኅልውና ቀጣይነት (ለሉዓላዊነቷ)፤ ለዜጎቿ አንድነትና ትብብር፤ ብሎም ለዕድገታቸው ማረጋገጫና ለአንድነታቸው መተማመኛ ሆኖ ሊታይም ይችላል። ምናልባትም በዴሞክራሲ ሥርዓትና ሂደት ሕዝቡ ወደፊት ለሚያዘጋጀው ሕገ-መንግሥት እንደማጣቀሻ/አመልካች ሆኖ የማገልገል ሚና ይኖረውም ይሆናል። አንዳንድ ሀገራት እንደዚህ ዓይነቱን ሰነድ፤ እንደ ሀገራዊና ታሪካዊ ተቋም ተቀብለው አክብረው ይኮሩበታል። ማግና ካርታ እንደ ዓብነት ቢጠቀስ ስህተት አይሆንም።

ለዚህ ሁሉ ሃላፊ የሚሆነው ግን ሀገራዊ ተቋም ነው። እስካሁን ይህንን የሚያንፀባርቅ ኢትዮጵያዊ ተቋም የለም። በታሪክ፤ እንደ ሀገራዊ ተቋማት ሆነው፤ በማዕቀፍ ደረጃ ሕዝቡን ሲያስተባብሩ የነበሩት የሃይማኖትና የታሪክ ተቋማት ነበሩ። እነርሱም ሆን ተብሎ እንዲጠፉ ወይም እንዲዳከሙ ተደርገዋል። የሀገር ተቆርቋሪ ተቋማት አለመኖር ደግሞ፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ፤ የጠላቶቿ ጥፋት መለማመጃ ዒላማ አድርጓታል።

የሀገሪቱን ጥቅም የሚያስጠብቅ ሰነድና ተቋም መመስረት አስፈላጊነቱ፤ በጊዜና በቦታ ወይም በትውልድና የመንግሥት ሥልጣን ለመያዝ በሚደርግ የምርጫ ውድድር ወቅት የሚወሰን አይደለም። ከሀገሪቱ የረዥም ጊዜ ጥቅምና ዘለቄታዊ ራዕይ አኳያ መታየት ይኖርበታል። እስካሁን ድረስ ይህ በሰፊው የታሰበበት ለመሆኑ ዕርግጠኞች አይደለንም። የድርጅቶች የፖለቲካ ፕሮግራም ግን ከመንግሥት ሥልጣን አያያዝ ባሻገርና ስለ ሀገሪቱ ስትራተጂያዊ ራዕይና ጥቅም ብዙም የሚጨነቅ ለመሆኑ ማንም ዜጋ ዕርግጠኛ አይደለም። በሆነው መንገድ የመንግሥት ሥልጣን የጨበጠ የአገዘዝ ቡድን ሁሉ፤ ሀገርንና ሕዝብን እየነዳ ወደሚሄድበት ይሄዳል እንጅ ምንም ዋስትና አይኖረውም። የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ መተማመን የሚገባው እራሱ ተስማምቶ፤ መክሮ ዘክሮ በሚመሰረተው ሀገራዊ ተቋም ብቻ ነው። ይህ ተሟልቶ ሲገኝ በርግጥም ሕዝብ የራሱን መንግሥት በመገንባት፤ መሪዎችንም እየመረጠና እየተቆጣጠረ ራሱን የማስተዳደር ኃይልና ሥልጣን ይኖረዋል።
የጅምላ አመለካከትና አስተሳሰብ የሚያስከትለው ችግር ሁሉንም በአንድ ሙቀጫ አስገብቶ የመውቀጥ አባዜ ነው። የቆየው ትውልድ አሁን ያለውን ትውልድ ሲረግምና ሲያወግዝ፤ ያሁኑ ትውልድም በበኩሉ ያለፈውን ትውልድ ሲከስና ሲነቅፍ ሁለቱም ሳይጣጣሙ እየቀሩ አንዱ ከሌላው የሚማርበት ዕድል ተዘግቶበት ይኖራል። በመሀሉ የሚጎዱት ሀገርና ሕዝቦች ይሆናሉ። ጉዳቱ ግን በዚህ በአሁኑ ትውልድ ላይ ብቻ አያበቃም። ሀኬቱ ወደ ሚቀጥለው ትውልድም ይተላለፋል። መከራና ችግርን ለተከታዩ ትውልድ ማስተላለፍ ደግሞ የታላቅ ሕዝብ ምልክት ሊሆን አይገባውም። ስትራተጂያዊ ራዕይ፣ ብሩኅና ተስፋ ያነገቡ የሀገር መሪዎች፤ ለሕዝባቸው መፃዒ ዕድል አርቆ በማሰብ ሁለንተናዊ ዝግጅት ከማድረግ አይቆጠቡም። ይህን ዓይነት ስብዕና ያላቸው ዜጎች "ከእኔ በኋላ መጭው ትውልድ ይጨነቅበት" ከሚሉት ራስ ወዳድ

መሪዎች በእጅጉ ይለያሉ። የራስ ወዳድ መሪዎች የሥልጣን ዘመናቸው እየረዘመ በሄደ መጠን ችግሩ እየተባባሰ መሄዱን ይቀጥላል። የዚህ ሁሉ ውስብስብ ድምር ውጤት ደግሞ፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ ባለቤት ያጣች ሀገር መሆኗ ነው። በኛ አስተሳሰብ እንኳንስ ለነገው ለዛሬውም እንኳ የሚያስቡ ዜጎችና ተቋማት ያጣች ሀገር መሆኗን የሚረዱ ክፍሎች የላትም ወይ የሚል ጥያቄን በየቦታው መጫሩ የሂደት ጉዳይ እንጂ የማይቀር ክስተት ነው።

በዚህ ሂደት መካከል የሚጠቀሙት ደግሞ ባዕዳንና የነርሱ አጋልጋይ የሆኑት አገር- በቀል የሀገራችን ጠላቶች ናቸው። ወያኔዎችም የመጀመሪያውን ረድፍ ይዘዋል። ትውልዱን በዘር፤ በቋንቋና በሃይማኖት እየከፋፈሉ ግርግርና ውዥንብር በመፍጠር ተጠቃሚዎች ሆነዋል። አሁንም ሆነ ወደፊት፤ ሕዝብ ተባብሮ በአንድ ላይ ካላመፀ፤ ይህ ዘረኛ ሥርዓት ይወገዳል ብሎ ለማመን ያስቸግራል። ይህ ማለት ግን፤ "ግንቦት ያመጣውን ግንቦት እስኪመልሰው ድረስ፤ እጅ -እግርን አጣጥፎ መቀመጥ ተመርጧል ማለት አይደለም። ሕዝብ የሚበጀውን እራሱ አውቆ የራሱን ውሳኔ ሊወስድ ይችላል የሚለው አግባብነት ያለው ቢሆንም፤ ሕዝቡ ለሚወስደው ርምጃ፤ ግንባር- ቀደም ሚና መጫወት የነበረባቸው ለሕዝብ ነፃነት እንታገላለን ብለው ያወጁት ተቃዋሚ ድርጅቶች ናቸው ። ጥረት አላደረጉም ማለት ባይቻልም፤ የረባ ውጤት ግን እስካሁን አልተመዘገበም።

ዘወትር፤ የራሳችንን ድክመትና እንዝህላልነት ብሎም፤ ውጤት አልባ የመሆን ምክንያት፤ የባዕዳን እጅ አለበት ማለቱ ብቻ ለመፍትሄ ፍለጋችን ብዙም ሊጠቅመን ባይችልም፤ የሀገራችንን የጥፋት ዕቅድ ፤ ከመጀመሪያው አንስቶ የነደፉት ያውሮፓ ቅኝ ገዥዎች እንደነበሩ ግን መካድ አይቻልም ። ይህንንም ዕቅድ፤ በሀገራችንም ላይ በሥራ ለመተርጎም ሞክረው አልተሳካላቸውም። በብልሆቹ አባቶቻችን ጀግንነት ተጨናገፈባቸው።

ባለመታደልና በዚህም ትውልድ እንዝኅላለነት ምክንያት፤ ወያኔዎቹ በትክክል በተግባር ተረጎሙት። ወያኔዎቹ እቅዳቸው ሰለተሳካላቸው፤ ተጠቃሚዎች ሆነዋል። ዕቅዱንም፤ በተግባር ለመተርጎም የሚያስችላቸውን ሁለንተናዊ ትብብር ከባዕዳኑ አግኝተዋል። የገንዘብ፤ የመሳሪያ፤ የቁሳቁስ፤ የዲፕሎማቲክና የፕሮፓጋንዳ እርዳታ ሁሉ ተለግሶላቸዋል። ይህንን ማግኘታቸው ማንንም አላስደነቀም። ምክንያቱም፤ ከባእዳን ጠለቶቻችን ጋር ባንዳዊ አገልግሎት በመፈፀማቸው ነበር። ሕዝብን ከድቶ፤ ሀገርንም ሸጦ ከባዕዳን ጋር ተመሳጥሮ፤ ምንሊክ ግቢ መግባት፤ ውርደትን እንጅ ክብርን አላስገኘላቸውም። የሕዝብን ጥላቻና ተቃውሞ እንጅ አድናቆትን፤ ከበሬታንም ሆነ ይሁንታን አላተረፈላቸውም። ወያኔዎች፤ በግንቦት ወር ይሁን በመስከርም ወር መጡ ልዩነት የለውም። በዕዳን አለቆቻቸውም፤ እንኳን ደስ አላችሁ በማለት ግን ይተባበሯቸዋል። ጠላት፤ ምን ጊዜም ጠላት ነው። ባዕዳንም፤ ይህን አገር በቀል ቡድን፤ ለራሳቸው ጥቅም ማስጠበቂያ ይጠቀሙብታል። በትውልድና በዜግነት አሁን በሥልጣን ላይ ያሉት ግለሰቦች፤ ኢትዮጵያውያን ሊሆኑ ይችላሉ ቢባሉም፤ በመንፈስና በተግባር ግን ባዕዳን በመሆናቸው የኢትዮጵያን ሀገራዊ ጥቅም ያስጠብቃሉ ተብለው አይታሙም። ሊወቀሱም የሚችሉ አይሆኑም። ምናልባት፤ ተውቃሾች የምንሆነው እራሳችን ነን። ምክንያቱም፤ "ከሞኝ በራፍ ብልሆቹ ሞፈር ሲቆርጡ" ዝም ብለን ተመልክተናቸዋልና !

በዚህ ሐቅ ስምምነት ካለ፤ ወያኔን ከጨዋታው ውጭ በማድረግ ከኢትዮጵያ ሕዝብ መነጠል የመጀመሪያው ተግባር ሊሆን ይገባል። ይህ ደግሞ የማይቻል አይደለም። ውኅዳኑ ተባብረው፤ በርትተው አንድ ሆነው፤ ኢትዮጵያን ማፈራረስ እስከሚችሉ ድረስ ከተሳካላቸው፤ ሌላው ብዙሃኑ ተባብሮ አንድ ሆኖ ኢትዮጵያን ከጥፋት የማያድንበት አንዳችም ምክንያት አይኖርም። አሁን ሀገሪቱ ከገጠሟት ዓይነተኛ ችግሮች አንዱ፤ የምልዐተ- ሕዝቡ አለመተባበር ነው። ለዚህም አጥጋቢ ምክንያት አለ። ይህም የአምባገነንን ባኅርይ በቅጡ ያለመረዳት ደክመት ሆኖ ይገኛል። ደርግ ሥልጣን እንደያዘ ሰሞን "ሊወድቅ አንድ ሐሙስ ቀርቶታል" ሲባል እንደነበረው ሁሉ ወያኔ የትም አትደርስም፤ የሚለው ቀቢፀ-ተስፋ የትም

አላደረስም። ይህ አመለካከት ከቶውንም ትጥቅ አስፈች ነው። ወያኔዎቹ፣ የኢትዮጵያን ጀግኖች ታሪካዊ ስም እየተጠቀሙ፤ "ዘመቻ ቴዎድሮስ" "ዘመቻ ዋለልኝ" ብሎ በመቀበጣጠር፤ ቁማር ተጫውተዋል። አሁንም "እኛ ከሌለን፤ ሀገሪቱ ትፈርሳለች"፤ " እኛ ከሄድን አማራና ኦሮሞ" ይፈጅሃል"፤ የሚለውን እርካሽ ማስፈራሪያ ለምርጫ ዘዴያቸው አድርገውታል። ደግነቱ ግን ሕዝቡ ከነርሱ በላይ የነቃና የበቃ ሆኖ ለከይሲ ፕሮፓጋንዳቸው በቀላሉ ሰለባ ሊሆንላቸው አልቻለም።

እንዲያው በደፈናው ሕዝቡ ሊተባበር አልቻለም ብሎ መደምደም ግን፤ ትንታኔ ቢስ የሆነ የጅምላ ነባቤት ነው። የድርጅቶቹን ድክመት ወደ ሕዝቡ እንደማላከክም የቆጠራል። እንዲያው በደፈናው "ሕዝቡ ሊተባበር አልቻልም " ብሎ በመናገር የጋራ ችንፈትን እንጅ የጋራ ድልን መጎናፀፍ አንችልም ወደሚል ድምዳሜ ያስኬዳል። ይህ ደግሞ ተቀባይነት ሊኖረው የሚገባ አይሆንም። ሕዝቡ መተባበር የሚችልበትን መንገድና ብልኃት ፈልጎ የፖለቲካ ምኅዳርም ይሆን ሌላ ተመሳሳይ የማሰባሰቢያ መድርከ ማዘጋጀት መቻል ያለባቸው የፖለቲካ ድርጅቶችና የማኅበራዊ ስብስቦች ናቸው።

መሪ ሊወጣ የሚችለው ከድርጅቶችና ከሕዝብ ማዕከላት መሆኑ ከታመነበት፣ በዕርግጥም የሕዝብና የፖለቲካ ድርጅቶች የጥምረት ሂደትና ትግል፤ ብርቱ ሕዝባዊ አመጽን ሊያስከትል የሚችል ቋጠሮ መቋጠር ይቻላል። ይህ አባባል በነባቢት ደረጃ በግልቡ ሲመለከቱት፤ ማር የተቀባ መፈክር መስሎ ሊታይ ይችል ይሆናል። ከልብ አስበው ወደ ተግባር ለመተርጎም የሚያስችለውን እቅድ ነድፎ በትጋት ከተሰራበት ግን ወያኔን አንበርክኮ፤ ሀገሪቱን ከጥፋት ለማዳን ብዙ ጊዜ አይፈጅም።

ለአለፉት ሃያ አራት ዓመታት የተደረገው ጥረት ሁሉ ግን የታሰበውን ውጤት ሊያስመዘግብ አልቻለም። ለዚህ በቂ ምክንያቶች አሉ። ከውቂ-ደብልቂው ጫጫትና ከአስረሽ-ምችው ዳንኪራ ባሻገር፤ ጥልቅትና ምጥቀት ያለው ውይይት በማድረግ መሠረት ያለው የኅብረት ኃይል መፍጠር አልተቻለም። ፍላጎቱና ጥረቱ አልነበረም ለማለት ባይቻልም፤ ከመተባበር ይልቅ የመለያየቱና የመከፋፈሉ ሚዛን እያደፋ ሰላስቸገረ ነው ቢባል እንደ ቀላል ምክንያት ሊቆጠር አይችልም። በፖለቲካ ትግል የኃይል አሰላለፍ ሚና ዓይነተኛውን ስፍራ ስለሚይዝ፤ ለኃይል ሚዛን የሚሰጠው አስተጋብዖ ከፍተኛ ይሆናል። የኃይል ሚዛኑን ወደ ራሱ እንዲደፋ ካላደረገ የተቃዋሚው ክፍል፤ መልኅቅ እንዳጣ መርከብ እየዋዠቀ ይቀራል እንጅ ፋይዳ ያለው ሥራ ሊሠራ አይጠበቅበትም።

ደም ቋጥሮ የሚመጣ ሌላ ግንቦት እንዳይከሰትና ዘለዓለም የሚፈሠውንም የሀገራችን ደም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለማድረቅ ከተፈለገ፤ የኢትዮጵያውያን መሠረታዊ ችግራችን ምንጭ የሆነውን ማድረቅ እንደ መጀመሪያ የመከላካያ መስመር ተቆጥሮ መታየት አለበት። የጠላትን የጥንካሬ ምንጭ ለማድረቅ ደግሞ የራስን ወዝና ላብ ብቻ ሳይሆን፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ፣ የደም መሥዋዕት መክፈልንም እንደሚጠይቅ ግልፅ ነው። ምክንያቱም ያለ መሥዋዕት ስርየት አይገኝምና !

እኛ የምናከብራቸውና የምናመሰግናቸው ታህሣሣውያንና የካቲታውያን ጀግኖች ሰማዕታት አሉን። ብዛታቸው ስፍር-ቁጥር ስሌለው የሁሉንም ስም መዝግቦ የማስፈሩ ተግባር፤ የታሪክ መዛግብት ድርሻ ይሆናል። የሀገራችን ታሪክ አንፀባራቂ ከዋከብት ሆነው እንደሚታወሱ ግን ዕርግጠኞች ነን። የእነርሱን የተቀደሰ አርዓያ አንግቦ የተነሳ ትውልድም ኢትዮጵያ እንዳሏት እናውቃለን። በየዓመቱ መከራና መዓት የሚያመጣው ግንቦትም ፍትህ ርትዕ፣ ነፃነትና እኩልነት፣ ሠላም፣ ዴሞክራሲና ብልፅግና አንግበው በሚመጡ ታህሣሥና የካቲት ይተካል፡፡ ያን ለማምጣት ደግሞ ማንኛውንም መሥዋዕት የሚጠይቀውን ትግል ከማካሄድ ሌላ ምርጫ እንደሌለ እንረዳለን። ጊዜና ቦታ የማይሽረው የኛ ምርጫ ደግሞ ይኸው ብቻ ነው።

**የመጨረሻው አቸናፊም የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሚሆን አንጠራጠርም !**